INTERME

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS AUTHORITY

የውስጥመጻጻፊያ

ቁጥር፡ ም/ሥ/የአድ/24/396/07
ቀን፡ 24/10/2007

- ለ፡ ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት
- ለ፡ ገላን ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለ፡ መጋዘን አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ሂደት
- ለ፡ ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት
- ለ፡ ሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት
- ለ፡ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥራ ሂደት
- ለ፡ በመንግስት የተሰጡ መብቶች ማስፈጸሚያ የሥራ ሂደት

- ከ፡ ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
  አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ጉዳዩ፡- በ "S" ዲክለራሲዮን ተመዝግበው ወደ ቦንድድ መጋዘን የሚገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ የተጻፈውን ደብዳቤ ይመለከታል፣

የጉምሩክ ኘሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ በቁጥር 3.0/219/07 በቀን 20 ሰኔ 2007 ዓ.ም ወደ ቦንድድ መጋዘን የሚገቡ ዕቃዎች የትራንዚት ስነ-ስርዓት የተጠናቀቀበት እና የ"S" ዲ/ዮን ተሞልቶ መቅረብ እንደ ቅድመ ሁኔታ መቀመጡ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የ"S" ሰነድ ሲሞላ የተሟላ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ዋና ቅጂ ደጋፊ ሰነዶች ከጉምሩክ ዲ/ዮን ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አሰራር ቀድሞ ዋናው ቅጅ ሰነድ ማግኘት ለማይችሉ የቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚዎች ችግር እያጋጠማቸው መሆኑን ጠቅሷል፡፡

በዚህ መሠረት የ"S" ዲ/ዮን ጋር በተያያዘ ከዚህ የውስጥ ማስታወሻ ጋር በተያያዘው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም እያሳሰብኩ የተላከውን 1 ገጽ ደብዳቤ በአባሪነት ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ አያይዘን ልከንላችኋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣
- ለሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ም/ሥራ አስኪያጅ
  አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ቁጥር / Ref.No. 3.0/2/9/02
ቀን / Date 20 ሰኔ 2007

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡- በ "S" ዲክለራሲዮን ተመዝግበው ወደ ቦንድድ መጋዝን የሚገቡ ዕቃዎችን ይመለከታል

ወደ ቦንድድ መጋዝን የሚገቡ ዕቃዎች የትራንዚት ስነ ስርዓት የተጠናቀቀበት እና የ "S" ዲ/ዮን ተመልቶ መቅረብ እንደ ቅደመ ሁኔታ መቀመጡ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የ"S"_ሰነድ ሲሞላ የተሟላ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ዋና ቅጂ ደጋፊ ሰነዶች ከጉምሩክ ዲ/ዮን ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው መሆኑ ይታወቃል፤ይሁን እንጂ ይህ አሰራር ቀድሞ ዋናው ቅጅ ሰነድ ማግኘት ለማይችሉ የቦንድድ መጋዝን ተጠቃሚዎች ችግር እያጋጠማቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ስለሆነም ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ "S" ሰነድ ተመዝግበው የሚገቡ ዕቃዎች ላይ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል የደጋፊ ሰነዶች ኮፒ በመጠቀም ዲክለራሲዮን ሞልተው እንዲያቀርቡ እየተደረገ እንዲስተናገዱ እያሳወቅን የ"S" ሰነዱ ወደ "C" 4071 ሰነድ ከመቀየራቸው በፊት ኦርጅናል ደጋፊ ሰነዶች ከ"S" ዲ/ዮን ጋር ማያያዛቸው እየተረጋገጠ አገልግሎት እንዲሰጥ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

[signature] ገዛኸኝ
ም/ዋና ዳይሬክተር
የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና
ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

ግልባጭ

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ስነ ስርዓት ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤ/ክ/ድ/ዳይሬክቶሬት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን



ስልክ.ቁ. / Tel. 011-466 74 66
ፋክስ / Fax 011-466 82 44
ኢሜል / E-mail erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website WWW.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box 2559
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia